ለተጨማሪ መረጃ?

RainScapes Rewards ሪቤት ማመልከቻዎች፣ ዜና፣ እና ተጨማሪ መረጃ ይህንን ዌብ ሳይት ይጎብኙ፤

rainscapes.org

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ስላለ የጎርፍ ውሃ አስተዳደር፣ የውሃ ከለላ እና የውሃ ጥራት ጥበቃ መረጃ፣ ይህንን ዌብ ሳይት ይጎብኙ፤

montgomerycountymd.gov/stormwater

የ rainscapes.org ድረ-ገጽን ዛሬውኑ ይጎብኙ

DEPARTMENT OF
ENVIRONMENTAL PROTECTION
MONTGOMERY COUNTY • MARYLAND

255 Rockville Pike, Suite 120
Rockville, MD 20850
ለተጨማሪ መረጃ በ 311 ይደውሉ
www.montgomerycountymd.gov/311

(rev. 11/18)

RAINSCAPES REWARDS

ቤቶች እና የንግድ ተቋማት ለአካባቢ ተስማሚ በሆነ ላንድስኬፒንግ የጎርፍ ውሃ መጥለቅለቅን ለመቀነስ የሚረዳ

ሞንትጎመሪ ካውንቲ፣ ሜሪላንድ

RainScapes Rewards ምንድን ነው እናም ለርስዎስ ምን ያስገኝልዎታል?

RainScapes Rewards ፕሮግራማ ለሞትጎሞሪ ካውንወቲ ነዋሪዎች እና የንግድ ድርጅቶች የፋይናንስ ድጎማዎች እንዲሁም የቴክኒካዊ ድጋፍ አፈር ከንብረትዎ ላይ በጎርፍ ውሃ ታጥቦ (ወይም የዝናብ ውሃ እንዳይሄድብዎት) ወደ።

www.rainscapes.org በሚገኘው የሬይንስኬፕስ ዌብሳይት በመሄድ ለንብረትዎ መጠቀም የሚችሉትን የሪቤት መጠን ይወቁ።

RainScapes ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛሉ

የሬይንስኬፕስ መሬት አቀማመጦች ማዘጋጀ መንገዶች የውሃ ብክነትን ለመከላከል፣ የከርሰ ምድር ውሃን ለመሙላት እና የምንጮችን እና ወንዞችን ተፈጥሮአዊ ስርዓት በአንድ ጊዜ በአንድ ንብረት ላይ ለማስጠበቅ ያግዛሉ፡፡ እንዲሁም የውሃ ፍጆታ እና የሀይል ግልጋሎትን በመቆጠብ ገንዘብን ለማዳን እንዲሁም የንብረትዎን ዋጋ ለማሻሻል የተለያዩ የአማሩ ክፍሎን ለመጨመር ያግዛሉ፡፡

የጎርፍ ውሃ የሚያመጣው የአፈር መሸርሸር ችግር ምንድን ነው?

በከተማ ስፍራዎች- ጥርጊያ፣ የመኪና መንገዶች በጣሪያ አናት እና በመስክ ላይ የዝናብ ውሃ በቀላሉ ወደ ከርሰምድር ውስጥ አይዘልቅም በዚህ ፈንታ በጎርፍ ውሃ እየተሸረሸረ በመሄድ የከተማ አካባቢዎችን የሚበክሉ መርዛማ ነገሮች-በከርሰ ምድር ላይ ለእንክብካቤ አላማ የምንገለገልባቸው ተረፈ ኬሚካሎች ክምችቶች ፍርስራሽ እና ውድቅዳቂ ነገሮች እንዲሁም ከተሽከርካሪዎች የሚለቀቁ ፈሳሾች በቀጥታ በጎርፍ ውሃ መውረጃዎች አማካኝነት ወደ አካባቢው ምንጮች እና የውሃ አካላት ቀስ በቀስም ወደ ወንዞች ውስጥ ይዘልቃሉ፡፡

የጎርፍ ውሃ ፈጣን እና ከፍተኛ የመሻርሸር ብቃት ያለው በመሆኑ የመኖሪያ ስፍራችንን አነስተኛ የውሃ ምንጮችን ሕይወት አካላት በእጅጉ ይጎዳል፡፡ የጎርፍ ውሃ በሞንትጎሞሪ ካውንቲ ምንጮች እና በፖቶማንክ (Potomac) እንዲሁም አቱክስተን (Patuxent)ወንዞች ላይ ዋንኛውም የብክንት እና የተፈጥሮ መራቆት መንስኤ ነው፡፡

RainScapes Rewards

ማበረታቻዎችን እንዴት ማግኘት እንደምንችል

ለተመላሽ ክፍያዎች ብቁ የሚያደርጉ ንብረቶች በሞንት ጎሞሪ ካውንቲ ሜሪላንድ ከሮክቪ፣ ታኮማፓርክ እና ጌተርስበርግ ከተሞች መዘጋጃ ቤት ወሰኖች ውጪ የሚገኙት ንብረቶች በሙሉ ለተመላሽ ክፍያ ብቁ ናቸው፡፡

አመልካቾች የተመላሽ ክፍያ ማመልከቻ መሙላት አለባቸው፡-

በ rainscapes.org ድረ-ገጽ ስለሚከተሉት መረጃ ያገኛሉ:

1. የብቁነት መስፈርቶች
2. ለእያንዳንዱ RainScape አቀማመጥ አጠባበቅ ቴክኒክ የዲዛይን መስፈርቶች
3. የሳይት ፍተሽ ሂደትs
4. ሌሎች መስፈርቶች

አንላይን በዚህ ያመልክቱ፥:

rainscapes.org

RainScape ቴክኒኮችን ለግቢዎ ወይም ለንብረትዎ

ለጓሮ ወይም ለንብረትዎ ከዝናብ ማምለጫ መንገዶችን ያስቡባቸው የተለያዩ አይነት የመሬት አቀማመጦች አፈሩ የዝናብ ውሃ በጎርፍ መልክ ተሸርሽሮ ከሚወስደው ይልቅ RainScapes Rewards እዛው መጦ እንዲያስቀረው ለማድረግ ያስችላሉ፡፡ እነዚህ የመሬት አቀማመጦች፡-

የመሬት አቀማመጥ ዝግጅት ከሀገር በቀል ተክሎች ጋር ለማስጠበቅ እና ውድ የኬሚካል ግብአቶችን ለመጠቀም በጣም ብዙ ጊዜ የሚወስዱ ልማዳዊ የመሬት አጠባበቅ መንገዶችን ይተካል፡፡ እንዲሁም በዚህ ፋንታ የአትክልት ስፍራዎቹ ከአካባቢው የዝናብ ሁኔታዎች ጋር የተላመዱ፣ የድርቅ ወቅቶችን ለመቋቋም የሚችሉ እና ለንብረትዎ ያመረ ውበት ለማቅረብ የሚችሉ ሁኔታዎችን የሚለመዱ በቀላሉ ለመጠበቅ የሚችሏቸው ሀገር በቀል ዛፎች ተተክለዋል፡፡

ውሃ የሚገባባቸው ጥርጊያ መንገዶች የዝናብ ውሃ በጣም በፍጥነት ወደ ውስጥ ሰርጎ እንዲገባ እና በውስጡም በተፈጥሮአዊ መልኩ እንዲጣራ ወደሚያስችለው ከርሰ ምድር ውስጥ በመግባት የተለመደው በጎርፍ ውሃ ተሸርሽሮ ከሚወስደው የአፈር ክፍል በተለየ መልኩ አካባቢዎን ለማስጠበቅ ያስችልዎታል፡፡ ውሃ የማይገባባቸው አካላትን እንደ አርማታ ወይም የመኪና አስፋልት መንገዶችን ውሃ ከሚገባባቸው ጥርጊያዎች ጋር በአንድ ላይ ከጎርፍ ውሃ ማስጠበቅ፡፡

በዝናባማ የአትክልት ስፍራ ውስጥ ተክሎች በማንኪያ መሰል ቅስጥ ስፍራ በአንድ ልዩ የአፈር ድብልቅ ተሞልተው ይተከላሉ፡ ፡ይህ ማፈኛ ዝናብን ለመሰብሰብ እና ወደ ከርሰ ምድር ውስጥ ተጣርቶ እንዲገባ ያስችላል፡፡ በዝናባማ የአትክልት ስፍራ ውስጥ ሀገር በቀል ተክሎች ከጠንካራ፣ ጥልቅ ስር ካላቸው ተክሎች ጋር በአፈሩ ጥልቅ ርብራቦች ውስጥ ውሃን ለማጣራት እና ለማውረድ ሊያግዙም ይችላሉ፡፡

ጥርጊን ስለማስወገድ አንድ ውሃ የማይሰርግበበት አካባቢን ከመሸርሸር አደጋ ለመታደግ በጣም ቀጥተኛው ዘዴ ጥርጊያ መንገድን ማስወገድ ነው! ጥርጊያ መንገድ ከተወገደ በኃላ፣ አካባቢው ውሃ ከመሸርሸር ይልቅ መጦ ማስቀረት በሚችልበት መንገድ መዘጋጀት እና ተክሎች መልበስ አለበት፡፡

የውሃ ማጠራቀሚያ ማቴሪያል ወይም ሲስተም ከዝናብ ውሃ ማጠራቀሚያ በርሜል ተለቅ ያለ የውሃ ማቆሪያ ኮንቴነር ሲሆን ከከርሰ ምድር በላይ ወይም በከፊል ወይም በሙሉ በከርሰ ምድር ውስጥ ሊገኝም ይችላል፡፡ በውሃ ማጠራቀሚያ ማቴሪያሉ የተጠራቀሙ ውሃዎች የአትክልት ስፍራዎን፣ ወይም ሌሎች ተክሎችዎን ለማጠጣት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ በከፍተኛ መጠን የተነሳ እና በመሩት ውስጥ ለመቀበር ባለው አመቺነቱ አንድ የውሃ ማጠራቀሚያ የቦታ ውስንነት በሚኖርባቸው ስፍራዎች ላይ እጅግ በጣም አስተማማኝ የጎርፍ ውሃ መቀነሻ መንገድ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡ ግን ለታቀደው የውሃ ግልጋሎት እና የአጠባበቅ ፍላጎቶች ጥሩ እቅድ ማውጣት ይጠይቃል፡፡ የመጠጥ ውሃ ወይም ሌሎች ለቤት ውስጥ ውሃ ግላገሎት ላይ የሚውሉ ሌሎች ውሃዎች በአሁኑ ጊዜ በቧንቧ አሰራር ደንቦች አይፈቀዱም፡፡

ዛፎችን መትከል የዛፍ ጥላን ለመጨመር ያግዛል ቅጠሎቹ የዝናብ ጠብታዎችን ለማቋረጥ እና አስቀርተው መያዝ የጎርፍ ውሃ የሚያስከትለውን የመሬት መሸርሸር ይቀንሳሉ፡፡ ዛፎች እጅግ በጣም ሰፊ የከርሰ ምድር ስር ስርዓት ስላላቸው ወደመሬት ውስጥ የዝናብ ውሃን መጠው ለማስቀረት ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም የቤት ውስጥ የሃይል ፍጆታ ሂሳቦችን ለመቀነስ እና የንብረቱን ዋጋ እስከ 20 በመቶ ድረስ ለመጨመር እንደሚያስችሉ ታይቷል፡፡

የዝናብ በርሜል ከጣሪያ አናት ላይ የሚወርዱ የዝናብ ውሃዎችን ለመሰብሰብ እና ለማከማቸት የሚያገለግል ኮንቴነር ወይም ስርአት ነው የዝናብ በርሜሎች ውሃን ለማስጠበቅ፣ የጎርፍ ውሃ ከግል ንብረቶችዎት ላይ መሸርሸርን እንዳያስከትል የሚቀንሱ እና ለተለያዩ የመሬት ክፍል ግልጋሎቶች ነጻ ውሃን የሚያቀርቡ ናቸው፡፡

እነዚህን 7 የአሰራር ዘዴዎች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ከ RainScapes ድረ-ገጽ ያገኛሉ።

ደረጃ በደረጃ መመሪያዎች፤ የሪቤትና የተክሎች ዝርዝርን በተመለከተም ከ rainscapes.org ድረ-ገጽ ያውርዱ